# ሓጅና ዑምራ

## ኣድራጊዎች መመሪያ

# الحج والعمرة

تأليف : بحرو عمر



باللغة الأمهرية (الإثيوبية)

# ለሐጅና ዑምራ አድራጊዎች መመሪያ

ዝግጅት፦
ባህሩ ዑመር

አሳታሚና አከፋፋይ
አልተውባ መጻህፍት መደብር

بسم الله الرحمن الرحيم

አቅሙና ችሎታው ባላቸው አገልጋዬቹ ላይ የተከበረውን ቤቱን ካዕባን እንዲጎበኙ ግዴታ ላደረገውና እንዲሁም ሥራውን በአግባቡ ለፈጸሙ አገልጋዬቹ ኃጢያታቸውን ምሮ ማዕረጋቸውን ከፍ ለማድረግ ቃል ለገባው ኃያሉ አምላክ አላህ(ሱ.ወ) ምስጋና ይገባው:: የአላህን ቤት ከጎበኙ በሶፋና መርዋ መካከል ከተመላለሱና ለአላህ ጥሪ አዎንታዊ ምላሽ ከሰጡ ሰዎች ሁሉ በላጭና ምርጥ በሆኑት ነብያችን ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ላይ የአላህ ውዳሴና ሰላም ይሁን! ውድ ሐጃጅ ሆይ! በቅድሚያ ወደዚህ ወደ ተከበረውና ወደ ተባረከው ምድር ለመጓዝ ከታጩ ሰዎች መካከል አላህ ስላደረገህ እንኳን ደስ ያለህ እንላለን:: አላህ(ሱ.ወ) የሐጅና የዑምራ ሥራህን እርሱ በሚወደውና በሚፈልገው መልኩ ለማከናወን ያብቃህ! የምትሰራው ሥራ በሙሉ ለርሱ ብቻ ተብሎ የተሰራና የነብዩን(ሰ.ዐ.ወ) ሱና የተከተለ ያድርግልህ

ሥራህንም ተቀብሎ በመልካም ሥራ ሚዛንህ ላይ ያኑርልህ! አሚን! የአላህ እንግዳ የሆንከው ውድ ወንድማችን! ለማንኛውም ጉዞ መሪና አስተማሪ እንዳለው እሙን ነው ከማንም የተሰወረም አይደለም። ለዚህ ታላቅ ጉዞ ለዚህ ታላቅ መለኮታዊ ስደት መሪና አስተማሪው የነብያቶች ፊርጥ የሆኑት ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው ። የሐጃጆች መመሪያም "የሐጃችሁንና የዑምራችሁን አሰራር ከኔ ተማሩ" በማለት የተናገሩት ነብይ መመሪያና ደንብ ነው ። ከዚህ ነብያዊ አባባል በመነሳት ማንኛውም በሐጅ ወይም በዑምራ አማካይነት የአላህን ቤት ለመጎብኘት የሚነሳ ሰው ወደ ሥራው ከመግባቱ በፊት ይህን ነብያዊ መመሪያና ደንብ በትክክል ከተዘጋጁ መፅሀፎች ወይም በዘርፉ በቂ ዕውቀት ካካበቱ ዑለማዎች ላይ በሚገባ መማር ይኖርበታል ። ውድ ሐጃጅ ወገናችን ሆይ! ለሐጅህና ለዑምራህ

ስኬታማነት በማሰብ እነሆ! ይህችን አነስተኛ መፅሐፍ አዘጋጅተን ስናቀርብልህ እጅግ ከፍተኛ ደስታ ይሰማናል ::

**አዘጋጁ ወሳኝ ምክሮችና የጉዞ መሰናዶዎች**

ውድ ሐጃጅ ሆይ! በቀጥታ ወደ ሐጅና ዑምራው ሥርዓተ-አፈፃፀም ሁኔታ ከመግባታችን በፊት አንዳንድ ወሳኝ ምክሮችንና የጉዞ መሰናዶዎችን ልናስታውስህ እንወዳለን ::

1. ለሐጅና ለዑምራ ጉዞ የሚነሳ ሰው በመጀመሪያ ኒያውን ማስተካከል ይኖርበታል :: ይህም በሐጁ ወይም በዑምራው ጉራ፣ ቅፅል ስም፣ ዝና፣ ይዩልኝ፣ ይስሙልኝና ዓለማዊ ጥቅማ ጥቅም ሳይሆን ማሰብ ያለበት የአላህን(ሰ.ወ) ውዴታንና ፍቅርን ብቻ ነው ::

2.መንገደኛ የሆነ ሰው ኑዛዜውን በሚገባ መፃፍ፣ ያለበትን ዕዳና ለሰው ያበደረውን ገንዘብ መመዝገብ፣ የሰዎች አደራ እጁ ላይ ካለ መመለስ ወይም ባለቤቶቹ ከሐጅ

እስኪመለስ ድረስ ከራሱ ንብረቶች ጋር ንብረታቸውን እንዲቀይ መፍቀዳቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል ። ምክንያቱም የመሞቻ ጊዜያችን ያለው በአላህ/ሱ..ወ/ እጅ ነውና ።

3. ከሰራነው ኃጢአት ወደ አላህ መመለስ(ተውበት ማድረግ)፣ ከዚህ በፊት ባሳለፍነው ኃጢአት መፀፀትና ዳግም ወደዚያ ኃጢአት ላለመመለስ መወሰን ።

4. ሰዎችን በድለን ከሆነ መካስ ለምሳሌ የሰው ክብርን ካጎደፍን ይቅርታ መጠየቅ ወይም የሰው ገንዘብ ከወሰድን የወሰድነውን ገንዘብ መመለስ ወይም መመለስ ካልቻልን ይቅርታ መጠየቅ።

5. ለሐጅና ዑምራችን ጉዞ የሚሆነንን ንፁህ(ሀላል) ገንዘብ ማዘጋጀት ምክንያቱም አላህ ንፁህ ነውና። ንፁህን እንጂ አይቀበልም።

6. ከኃጢአት ሁሉ ፍፁም መራቅ፣ ማንንም በምላስም ሆነ በእጅ አለማስቀየም ሐጃጆችንም

ሆነ ዑምራ ፈፃሚዎችን ከመግፋት ከመረጋገጥ መጠንቀቅ፣ ነገር ከማዋሰድና ሰው ከማማት መታቀብ፣ በማንኛውም ጉዳይ ከጓደኛም ጋር ሆነ ከሌሎች ሰዎች ጋር አለመነታረክ፣ ውሸት ከመናገርና በአላህ ላይ የማያውቁትን ነገር ከመዘላበድ መቆጠብ::

7.ግዴታ የሆኑብንን ነገሮች በሥርዓቱ መወጣት ለምሳሌ:- ሶላትን ወቅቱን ጠብቆ በጀመዓ መስገድ እንዲሁም ሌሎች መሰል ግዴታዎችን በአግባቡ መፈፀም፣ ዒባዳ ማብዛት ለምሳሌ ቁርዓን መቅራት፣ ዚክር፣ ዱዓ ማድረግ፣ በጥሩ ማዘዝ፣ ከመጥፎ መከልከል፣ ለሰዎች በድርጊታችንም ሆነ በንግግራችን መልካም መዋል፣ ችግረኞችን መርዳት፣ ለሙስሊም ወገኖቻችን መራራት፣ ለደሀዎች ሰደቃ መስጠት ... ወዘተ

8.ለጉዟችን ጥሩ ጓደኛ ሙምረጥ

9. የጥሩ ሥነ-ምግባር ባለቤት መሆን ሰዎችን በጥሩ ፀባይ መቅረብ ገራገርነትን ፣

ቻይነትን ፣ ይቅርባይነትን ፣ዓይናፋርነትንና ሌሎች መሰል ባህሪያትን መላበስ

10. ቤተሰቦቻችንን አላህን እንዲፈሩ፣ ትዕዛዙን እንዲፈፅሙና የከለከላቸውን ነገር ሁሉ እንዲርቁ አደራ ማለት

11. ከረሱል(ሰ.ዐ.ወ) የተገኙ ዱዓዎችንና ዚክሮችን በተቻለ መጠን ማጥናት በተለይ መጓጓዣ ላይ ስንወጣና ስንወርድ የምንላቸውንና እንዲሁም በሐጅ ሥራችን ላይ የምንጠቀምባቸውን ዚክሮች በቃል መሸምደድና ትርጉማቸውንም ማወቅ::

12. ይህ ጉዞ የተባረከና ወደ ጌታችን ወደ አላህ (ሱ.ወ) የምናደርገው ጉዞ መሆኑን፣ ጉዞው አላህን በብቸኝነት በማምለክ ሥራን ለርሱ ብቻ በማድረግ ለጥሪው አዎንታዊ ምላሽ በመስጠትና እርሱን በመታዘዝ ምንዳውን በመከጀልና መልዕክተኛውን

(ሰ.ዐ.ወ) በመታዘዝ ላይ የተመሰረተ ጉዞ መሆኑን በልቦናችን ላይ ዘወትር ማሰብ

13. አላህ በኛ ላይ ግዴታዎችን(ፈርድ ነገሮችን) ደንግጓል እንዲሁም አጅራችን እንዲበዛ ብሎ ደግሞ በተጨማሪነት ሱናዎችን ደንግጓል:: አላህ ግዴታዎችን ካልፈፀመ ሰው ላይ ሱና ነገሮችን በፍፁም አይቀበለውም:: እጅግ በርካታ ሐጃጆች ይህንን እውነታ በመዘንጋት ሐጅሩል አስወድን ለመሳም ወይም ጠዋፍ ላይ ሶምሶማ ለመሮጥ ወይም ከመቃሙ ኢብራሂም ኋላ ለመስገድ አልያም ዘምዘም ለመጠጣት ሲሉ አማኝ ወንድሞቻቸውንና እህቶቻቸውን በመረጋገጥና በመግፋት ለከፋ አደጋ ይዳርጋሉ:: ከላይ የጠቀስናቸው ነገሮች ሱና ናቸው:: ሙስሊምን አዛ ማድረግ/ማስቃየት/ና በርሱ ላይ ጉዳት ማድረስ ደግሞ ሀራም ነው:: ታዲያ ሱና ለመሥራት ብለን ሀራም ነገር እንዴት እንፈጽማለን? ስለዚህ:- አላህ ይዘንልንና

አማኝ ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን በምንም ዓይነት መልኩ አዛ ከማድረግ/ከማሰቃየት/ እጅግ ልንጠነቀቅ ይገባል።

14. ወንዶች በተከበረው መስጂድ ውስጥ በተቻለ መጠን አማራጭ እያላቸው ከሴቶች ጎን ተሰልፈው መስገድ ፈፅሞ አይገባቸውም። ሴቶቹም ቢሆኑ አላህን ፈርተው ከኋላ ነው መስገድ የሚገባቸው።

15. በመስጂደል ሀራም መተላለፊያዎችና መግቢያ በሮች ላይ ሶላት መስገድ ተላላፊ ሐጃጆችንና ሰጋጆችን አዛ ማድረግ ስለሆነ ከዚህ ዓይነቱ ድርጊት መቆጠብ

16. ማንኛውም ሃይማኖታዊ ጉዳይ (ስለ ሐጁም ሆነ ሌላ) ካልገባችሁ አላህ "ያላወቃችሁ እንደሆነ የዕውቀት ባለቤቶችን ጠይቁ" ባለው መሠረት ዑለማዎችን ጠይቁ

17. በካዕባ ዙሪያ በመቆመጥ ወይም አጠገቡ በመስገድ ወይም ደግሞ ሀጀሩል አስወድና መቃሙ ኢብራሂም አጠገብ

በመቆም ጠዋፍ አድራጊዎችን አለማደናቀፍና ጠዋፋቸውን አለማወክ::

በመጨረሻም ለሁሉም ሐጃጆች የቁርዓንና የሀዲስን መመሪያዎች አጥብቀው እንዲይዙና አንዳንድ አላዋቂዎችን በመከተል አላስፈላጊ ሥራዎች ውስጥ እንዳይገቡ አጥብቀን አደራ እንላለን::

<u>ሐጅን ግዴታ (ዋጂብ) የሚያስደርጉ ነገሮች</u>

በወንዶችም ላይ ይሁን በሴቶች ሐጅን ግዴታ የሚያስደርጉ አምስት/5/ የጋራ ሸርጦች (ቅድመ ሁኔታዎች )አሉ እነሱም

1. ሙስሊም መሆን
2. ጤነኛ መሆን (የአዕምሮ በሽተኛ አለመሆን)
3. ለአካለ መጠን መድረስ
4. ነፃ ሰው መሆን (ባሪያ አለመሆን)
5. ሐጅን ሊያስደርግ የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ አቅም መኖር ለሴት ሐጅ አድራጊ አብሯት የሚጓዝ መሕረም (ባለቤቷ ወይም በጋብቻ ፈጽሞ ሊገናኛት የማይችል

የቅርብ ዘመዷ) መኖር በተጨማሪ መስፈርትነት ይጠቀሳል። መሕረም ሆኖ ይዟት መሄድ የሚችለው ግለሰብ በራሱ የሚከተሉትን መስፈርቶች ያሟላ መሆን አለበት።

ሀ ሙስሊም መሆን

ለ ጤናማ አዕምሮ ያለው

ሐ ለአቅመ አዳም የደረሰ መሆን

## የሐጅ ማዕዘናትና ግዴታዎች

የሐጅ አርካኖች(ማዕዘናት)አራት ሲሆኑ ሐጃጁ ከነዚህ ማዕዘናት አንዱን ከተወ ሐጁ ውድቅ ነው የሚሆነው ሌላ ሐጅ እንደገና የማድረግ ግዴታ ይኖርበታል። እነሱም:-

1. ኢሕራም ማድረግ 2. አረፋ ላይ መገኘት

3. ጠዋፈልኢፋዷ እና 4. ሠዕይ ናቸው

የሐጅ ግዴታዎች (ዋጂባት) ሰባት /7/ ሲሆኑ ሐጃጁ ከነዚህ ግዴታዎች አንዱን ቢተው መካ ከተማ ውስጥ ታርዶ

ለከተማይቱ ድሆች የሚከፋፈል ፊድያ(ቤዛ) የማቅረብ ግዴታ አለበት። ከሚታረደው እንስሳ ሥጋ ላይ ምንም ነገር መብላት አይፈቀድለትም ቤዛውም 1/7ኛ ግመል ወይም 1/7 ከብት አሊያም ለኡዱሂያ ዕርድ የሚያብቃቃ አንድ በግ/ፍየል/ ነው። እነዚህ ሰባት/7/ የሐጅ ግዴታዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. ለኢሕራም ማድረጊያ የተወሰኑት ሥፍራዎች (ሚቃቶች) ላይ ኢሕራም ማድረግ

2. የአረፋ ዕለት ዐረፋ ምድር ላይ ጀምበር እስክትጠልቅ ድረስ መቆየት

3. 10ኛውን ሌሊት ሙዝደሊፋ ማደር

4. የአያመትተሸሪቅ ሌሊቶችን ሚና ማደር

5. ጀመራቶቹ (ጠጠር መወርመሪያዎቹ) ላይ ጠጠር መወርወር

6. 10ኛው ቀን ላይ ፀጉርን መላጨት ወይም ማሳጠር

7. የመስናበቻ ጠዋፍ (ጠዋፈል ወዳዕ) ማድረግ ናቸው::

## የሐጅና የዑምራ ሥራዎች አፈፃፀም ሂደት

ውድ ሙስሊም ሆይ! የሐጅ ሥርዓት ሦስት ዓይነት የአፈፃፀም ሁኔታዎች አሉት:: ማንኛውም ሐጅ አድራጊ ከሶስቱ መንገዶች በአንዱ መንገድ ሐጁን ካከናወነ (ከፈፀመ) የሐጅ ግዴታውን በአግባቡ ተወጥቷል:: እነሱም ተመቱዕ፣ ቂራንና ኢፍራድ በመባል ይታወቃሉ ::

1.አት-ተመቱዕ :- አትተመቱዕ ማለት በተከበሩት የሐጅ ወራቶች

لبيك عمرة متمتعا بها إلى الحج

«ለብበይከ ዑምረተን ሙተመቲዐን ቢሃ ኢለልሐጅ» (ዑምራ አድርጌ እስከ ሐጅ ድረስ ነፃ ልሆን (ልፈታ) አቤት ብያለሁ) በማለት ለዑምራ ኢሕራም (ኒያ) አድርጎ የዑምራን ሥራ አከናውኖ ሲያበቃ ከዑምራው ይፈታና ነፃ ይሆናል :: ከዚያ በዙልሂጃ 8ኛው ቀን

ላይ ካለበት ሥፍራ /ከመካም ይሁን ከአቅራቢያው/ ለሐጅ ኢሕራም (ኒያ) ማድረግ ነው ::

2.አልቂራን :- አልቂራን ማለት

لبيك عمرة وحجا

«ለብበይከ ዑምረተን ወሐጅን»

(ለሐጅና ለዑምራ አቤት ብያለሁ) ብሎ በሐጅ ጊዜያቶች ለሐጅና ለዑምራ ኢሕራምን በአንድ ላይ አጣምሮ ማድረግ ነው :: ቂራን ያደረገ ሰው ከሐጁም ይሁን ከዑምራው የሚፈታው (ነፃ የሚሆነው) የማረጃው ቀን ላይ ብቻ ነው:: እስከዚያ ድረስ የኢሕራም ልብሱን እንደለበሰ በኢሕራም ላይ ይቆያል ::

3.አልኢፍራድ :- አልኢፍራድ ማለትለሐጅ ብቻ ኢሕራም ማድረግ ሲሆን ሐጃጁም ሚቃት (የኢሕራም ማድረጊያ ስፍራ) ሲደርስ

لبيك حجا

«ለብበይከ ሐጀን» (ለሐጅ ሥራ ብቻ አቤት ብያለሁ) በማለት የሐጅ ስራው ውስጥ ይገባል ከዚያ መካ እንደደረሰ የመግቢያ

ጠዋፍና ሰዕይ (በሶፋና መርዋ መካከል ምልልስ) ያደርጋል። ከዚያ ሌሎቹን የሐጅ ሥራዎች እስኪያከናውን ድረስ የኢሕራም ልብሱን እንደለበሰ በኢሕራም ላይ ይቆያል ።

በአንደኛውና በሁለተኛው መንገድ ሐጅንና ዑምራውን ያከናወነ ሰው በ10ኛው ቀን ዕርድ የማረድ ግዴታ አለበት ካልቻለ 10 ቀን ይፆማል ሶስቱን (3) ቀናት በሀጅ ሥራ ላይ እንዳለ ሲፆማቸው ሰባቱን(7) ደግሞ ወደ ሀገሩ ሲመለስ ይፆማል ።

ከሦስቱ የሐጅ መፈፀሚያ መንገዶች «ተመቱዕ» በላጭ ነው። ምክንያቱም ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) በሐጃቱልወዳዕ(በመሰናበቻው ሐጅ) ላይ የሚታረድ እንሰሳ ይዘው ላልመጡ ሰሀባዎች ያዘዟቸውና የመረጡላቸው መንገድ ነበርና ።

## ኢሕራም

ኢሕራም ከሐጅና ዑምራ ሥራዎች ውስጥ የመጀመሪያውን ሥፍራ ይይዛል ። ኢሕራም ማለት በሐጅ ወይም በዑምራ ሥራ ውስጥ መግባታችንን የምንገልፅበት ቃል ወይም ኒያ ነው ።

ለሐጅ ወይም ለዑምራ ሥራ የተነሳ ሰው ኢሕራም ውስጥ ከመግባቱ በፊት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይገባዋል ።

ሀ. ጥፍርን መቁረጥ ቀድሞ ቀመስን (የላይኛ ውን ከንፈር ፂምን) ማሳጠር የብብትንና የብልትን ፀጉር ማስወገድ

ለ. ገላን ከተመቸ ሙሉ በሙሉ መታጠብ። መታጠብ ካልተቻለም ሱና ስለሆነ ችግር የለውም። ለሐጅና ዑምራ የተነሱ ሴቶችን የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም ከዚህ ትጥበት አያግዳቸውም።

ሐ. ወንዶች ማንኛውንም የተሰፋ ልብስ ማለትም

እንደ ሱሪ ሸሚዝ ፓንት ቲሸርት ... ወዘተ በሙሉ ከአካላቸው ላይ ማስወገድ ይኖርባቸዋል፡፡

መ. ሴቶች ከዓይነ-ርግብ (ኒቃብ) ከመስከንተሪያና

ከጓንት ውጪ ያሉ ልብሶች በሙሉ ይፈቀድላቸዋል፡፡ ሐጃጇ ፊቷን ዐጅ ነብይ ወንዶች ያዩኛል ብላ ከሰጋች ዐጅ ነብዮቹ (ባዕድ ወንዶቹ) ከአቅራቢያዋ እስኪያልፉ ድረስ ብቻ በጅልባቧ ወይም በሻሿ መሸፈን ትችላለች ባትሸፈንም ደግሞ ወንጀል የለባትም፡፡

ሠ.ሐጃጁ ወይም ዑምራ አድራጊው ገላውን ከታጠበ

በኋላ ሰውነቱን ብቻ ሽቶ ይቀባል፡፡ የኢሕራም ልብሱን ግን መቀባት የለበትም፡፡ ለሴቷ ሽታው ጐልቶ የማይወጣ ሽቶ ብትጠቀም ይፈቀድላታል ችግር የለውም፡፡

ረ. ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ከፈፀመ በኋላ ከሶስቱ የሐጅና የዑምራ መፈፀሚያ

መንገዶች አንዱ ውስጥ ለመግባት ወይም የሚሰራው ዑምራ ብቻ ከሆኑ ዑምራ ለመሥራት ኢሕራም ካደረገ በቃሉ እንኳን ባይናገር ኢሕራም ውስጥ ገብቷል። ኢሕራም ላይ ድምፅን ከፍ ማድረግ ለወንዶች ሱና ነው። ለሴቶች ግን ለራሳቸው ብቻ በሚሰማ መልኩ ቢሉት ይመረጣል። ኢሕራም ከፈርድ ሰላት በኋላ ቢሆን ጥሩነው ወቅቱ የፈርድ ሰላት ወቅት ካልሆነ ደግሞ ውዱዕ አድርጎ የውዱዕ ሰላት ከሰገደ በኋላ ቢሆን ይመረጣል። በነገራችን ላይ ለኢሕራም ብቻ ተብሎ የተለየ ሰላት እንደሌለ ሊታወቅ ይገባል።

## ኢሕራም ላይ ያለ ሰው ሊርቃቸው የሚገቡ ነገሮች

ማንኛውም ሐጅ ወይም ዑምራ አድራጊ ከኢሕራም በኋላ የሚከተሉትን ነገሮች መፈፀም በርሱ ላይ ሀራም ይሆንበታል ::

1. ከመላ ሰውነቱ ላይ አንዲትንም ፀጉር ቢሆን እንኳ መንቀልና ጥፍርን መቁረጥ ረስቶ ወይም ባለማወቅ ፀጉርን ቢያሳጥር ወይም ቢላጭ ወይም ደግሞ ሲያበጥር በድንገት ፀጉሩ ቢረግፍ ወይም ቢነቀል ምንም ዓይነት ከፋራ(ቅጣት) የለበትም ::

2.ለሙሕሪም (ኢሕራም ላደረገ ሰው) ኢሕራም ከማድረጉ በፊት ተቀብቶት የነበረው ሽቶ ቅሪት ሽታ ካልሆነ በስተቀር ከኢሕራም በኋላ ሰውነቱም ሆነ ልብሱ ጥሩ ሽታ እንዲኖረው ብሎ ሽቶ መቀባት አይፈቀድለትም ምናልባት የኢሕራም ልብሱ ከኢሕራሙ በፊት ሰውነቱን ሽቶ ሲቀባ ሽቶ ቀብቶት ከሆነ የኢሕራም ልብሱን የግድ ማጠብ ይኖርበታል ::

3. ማንኛውም ሙስሊም ሙሕሪምም ይሁን አይሁን ወንድም ይሁን ሴት በሀረም (በመካ)

ክልል ውስጥ ማንኛውንም የዱር አራዊት ማደን ማስደንበር ማሳደድና የዱር አራዊቶቹን ለማደን የተሰማራን ሰው መርዳት አይፈቀድለትም ::

4. ሙሕሪምም ሆነ አልሆነ በሀረም(በመካ) ክልል ውስጥ የሚገኙትን በተፈጥሮ የፀደቁትን ዛፎችንም ይሁን ሌሎች ዕፅዋቶችን መቁረጥ አይፈቀድለትም ::

5. ለማስተዋወቅ (ባለቤቱን አፈላልጎ ለመስጠት) ካልሆነ በስተቀር በሀረም ክልል የወደቁ ነገሮችን (ገንዘብ ወርቅ ብር ... ወዘተ) ማንሳት ለሙሕሪምም ይሁን ለሌላ አይፈቀድም

6. ሙሕሪም የሆነ ሰው ለራሱም ይሁን ለሌላ ሰው ማጨት የጋብቻ ውል መፈፀምና ሴቶችን(ሚስቱም ትሁን ሌላ) በስሜት መነካካትና መደባበስ አይፈቀድለትም ::

7. ሙሕሪም የሆነች ሴት ለእጆቿ ጓንት ለፊቷ ኒቃብ(አይነ ርግብ) መጠቀም አይፈቀድላትም ::

8.ሙሕሪም በኢሕራም ልብሱም ይሁን በሌላ እንደ ጥምጣም ባርኔጣ መሀረብና ሌሎች መሰል ነገሮች ራሱን መሸፈን አይፈቀድለትም ረስቶ ወይም ባለማወቅ ቢሸፍን ወንጀል የለበትም እንዳስታወሰ ወይም ህጉን እንዳወቀ ከራሱ ላይ በፍጥነት ማስወገድ ይኖርበታል ይህ ዕገዳ ሴቷን አይመለከትም ::

9.ሙሕሪም የሆነ ሰው የተሰፉ ልብሶችን ሙሉ ሰውነቱ ላይም ይሁን ከፊል የሰውነቱ ክፍል ላይ መልበስ አይፈቀድለትም ለምሳሌ:- እንደ ሙሉ ልብስ ሸሚዝ ካባ ሱሪ ሸፍን ጫማ . . .ወዘተ

ሙሕሪም የሚያሸርጠው ፎጣ ወይም ያልተሰፋ ሽርጥና መሰል ብትን ጨርቆችን ካጣ ሱሪ መልበስ ነጠላ ጫማ ቢያጣ ደግሞ ሸፍን ጫማ መጠቀም ይፈቀድለታል::

ከላይ የተጠቀሱትን የተከለከሉ ነገሮች ሆን ብሎ የፈፀመ ሰው (ቤዛ) ማቅረብ አለበት :: ይህም አንድ በግ ወይም ፍየል ማረድ ወይም ስድስት ሚስኪኖች ማብላት ወይም ሶስት

(3) ቀን መፆም አለበት የድርአራዊት የገደለ ግን በአምሳያው የቤት እንሰሳት ያርዳል ፡፡ ለጋብቻ ውል መፈጸም ማጩት ሀሜት ነገር ማወሰድና መሰል ነገሮች ከፉራቸው ተውበት ብቻ ነው ፡፡

## ኢሕራም ላይ ያለ ሰው መጠቀም የሚፈቀድለት

የእጅ ሰዓት፣ ኤርፎን (ማዳመጫ) ፣ ቀለበት፣ ነጠላ ጫማ፣ ቦርሳ፣ መነፅር፣ ቀበቶ ዣንጥላ፣ ሽፍን መኪና ውስጥ መግባት፣ እንደሻንጣ ፍራሽ ... ወዘተ እራሱ ላይ መሸከም ሰውነቱ ከቆሰለ መድኃኒት አድርጎ ፋሻ መጠቀም፣ የኢሕራም ልብሱን ማጠብ ፀጉሩንም ሆነ ገላውን መታጠብና ራሱን ማከክ ይፈቀድለታል ፡፡

## <u>የዑምራ አፈፃፀም ሥርዓት</u>

የኢሕራም ማድረጊያው ሥፍራ ላይ ስትደርስ ገላህን መታጠብ ከቻልክ ታጥበህ (ሱና ነው) ሰውነትህን ብቻ ሽቶ ቀብተህ ከዚያ ለኢሕራም ያዘጋጀሀቸውን ሁለት ልብሶች

ለብሰህ ለዑምራ « ለብበይክ ዑምረተን»
(ለዑምራ አቤት ብያለሁ ብለህ (ኒያ)
ታደርጋለህ ከዚህ በኃላ

لبيك اللهم لبيك لبيك لاشريك لك لبيك إن الحمد والنعمة
لك والملك لاشريك لك

«ለብበይክ አልላሁመለብበይክ ለብበይክላሽሪከ
ለከ ለብበይክ ኢነል ሀምደ ወንኒዕመተ
ለከወልሙልከ ላሽሪከ ለከ»
(ጌታዬ ደግሜ ደጋግሜ ለጥሪህ አቤት
እላለሁ ተጋሪ የለህም ምስጋና ፀጋና ንግስና
ላንተ ብቻ ነው ሽሪካ የለህም) ትላለህ ይህ
ተልቢያ በሚባልበት ወቅት ወንዶች
ድምፃቸውን ከፍ ሲያደርጉ ሴቶች ግን
በአነስተኛ ድምፅ ነው የሚሉት ኢሕራም
ካደረጉ በኋላ ተልቢያ ዚክርና እስቲግፋር
ማብዛት እጅግ የተወደደ ነው:: ዑምራ
አድራጊ ተልቢያውን ጠዋፍ እስኪጀምር
ድረስ ደጋግሞ ማለት ይችላል ተወዳጅ ሱና
ነው ወንዶች የሚለብሱት ልብስ ያልተሰፋ
ሽርጥና ፎጣ(ኩታ) ሲሆን ነጭ ቢሆን

ይመረጣል ፡፡ ሴቶች ግን ዘወትር የሚለብሱትን አለባበስ ነው የሚለብሱት ባይሆን የወንድ ዓይነት አለባበስ እንዲሁም ጌጣጌጣቸውንና ሰውነታቸውን የሚያሳይ አለባበስ በፍፁም አይፈቀድላቸውም ለሴቶች እንደወንዶች የተለየ ከለር(ነጭ) መልበሱ ሱና አይደለም ነገር ግን ነጭ መልበስ ሱና ነው ሳይሉ ነጭ ልብስ ቢለብሱ አይከለከሉም፡፡

መካ (መስጂደልሀራም) ስትደርስ ካዕባን ሰባት ጊዜ ትዞራለህ ዙሩን የምትጀምረው ከሀጀሩል አስወድ (ጥቁሩድንጋይ ) አጠገብ «አልላሁ አክበር» በማለት ሲሆን ከቻልክ ጅምሩ ላይም ሆነ በእያንዳንዱ ዙር «ሃጀሩል አስወድን» ለመሳም ወይም በእጅህ ነክተህ እጅህን ለመሳም ሞክር ካልቻልክ ከርቀት «አላሁ አክበር» ብለህ በእጅህ ምልክት ማሳየት (ሰላምታ መስጠት) ብቻ ሱና ነው እጅ አይሳምም፡፡ ጠዋፉ የሚያበቃውም እዚያው «ሀጀሩል አስወድ» አጠገብ ነው፡፡

በምትዞርበት( ጠዋፍ በምታደርግበት) ወቅት የፈለከውን ዚክርና ዱዓ ማድረግ ትችላለህ ፡፡ ቁርዓን መቅራትም ይቻላል ፡፡

ከሩክኑል የማኒ እስከ ሀጀሩል አስወድ ያለው ሥፍራ ላይ ስትሆን በእያንዳንዱ ዙር ላይ

ربنا اتنا فى الدنيا حسنة وفى الاخرة حسنة وقنا عذاب النار

«ረብበና አቲና ፊድዱንያ ሐሰነተን ወፊል አኺረቲሐሰነተን ወቂና ዐዛበንናር» (ጌታችን ሆይ የቀርቢቱን ዓለም መልካምን(ፀጋን) የመጨረሻይቱንም ዓለም መልካም(ገነትን) ስጠን ከእሳት ቅጣት ጠብቀን) ማለት ሱና ነው ፡፡ ሩክኑልየማኒን ከተመቸህ በእጅህ መንካት ሱና ነው ከነካህ በኋላ ግን እጅ አይሳምም ካልተቻለ ግን በርቀት ማመልከት (ሰላምታ መስጠት) ሱና አይደለምና ዝም ብለህ ዙሩን መቀጠል ነው የሚገባህ ፡፡ ጠዋፉን ስትጨርስ ከተመቸህ በርቀትም ቢሆን ከነብዩ ኢብራሂም (ዓ.ሰ) መቆሚያ ሥፍራ (መቃሙ ኢብራሂም) ኋላ ሁለት

ረከዓ ትሰግዳለህ እዚህ ሥፍራ ለመስገድ ካልተመቸህ በመስጅዱ ውስጥ የትም ሥፍራ ብትሰግድ ችግር የለውም ::

በመጀመሪያው ረከዓ ላይ ሱረቱል ካፊሩን በሁለተኛው ረከዓ ሱረቱል ኢኽላስን (ቁልሁወላሁአሀድ)ን መቅራት ይወደዳል ::

በዚህ ጠዋፍ ላይ ለወንዶች ብቻ ቀኝ ትከሻቸውን መግለጥ (አልኢድጢባዕ) ሱና ነው:: የአገላለጡ ሁኔታ የፎጣውን መሀል ይዞ ቀኝ ብብት ሥር በማስገባት አንዱን ጫፍ በጀርባ በኩል አንዱን ደግሞ በደረት በኩል በማሳለፍ የፎጣውን ሁለት ጫፎች ግራ ትከሻ ላይ ማድረግ ነው የመጀመሪያዎቹ ሶስት(3) ዙሮች ላይ ብቻ ሁኔታዎች ከተመቻቹ ለወንዶች ሮጥሮጥ ማለት(ሶምሶማ) ሱና ነው ::

ከላይ የተጠቀሰውን ካከናወንክ በኋላ ወደ «ሰፋ» አምራ:: ወደ ሰፋ በምታመራበት ጊዜ

إن الصفا والمروة من شعا ئر الله

«ኢንነሰፋወልመርወተሚንሸዓኢሪላሀ»
«ሰፋናመርዋ የአላሀ(ትዕዛዝ መፈፀሚያ) ምልክቶች ናቸው» የሚለውን የቁርዓን አንቀጽ እያነበብክ ኮረብታው ላይ ውጣ ከዚያም ፊትህን ወደ ካዕባህ አዙር ሶስት(3) ጊዜ «አልሐምዱሊላህ አልላሁ አክበር» በል ከዚያ ሁለት እጆችህን አንስተህ የሚከተለውን ዚክር እያልክ የፈለግከውን ዱዓ በብዛት አድርግ ዚክሩንና ዱዓውን ሶስት ጊዜ ማለቱ ሱና ነው ::

لا إله إلا الله وحده لاشريك له الملك وله الحمد وهو

على كل شيء قدير لا له الا الله وحده انجز وعده.

ونصر عبده وهزم الاحزاب وحده.

«ላኢላሀኢልለሏሁወሕደሁ ላሸሪከለሁ ለሁልሙልኩ ወለሁልሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር ላኢላሀ ኢልለሏሁ ወሕደሁ አንጀዘ ወዕደሁ ወነሰረ ዐብደሁ ወሀዘመል አሕዛበ ወሕደሁ» (ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም እሱ ብቸኛ ነው ለርሱ ተጋሪ የለውም ንግስና ለርሱ ብቻ ነው

ምስጋናም የርሱ ነው እርሱ በነገሩ ላይ ሁሉ ቻይ ነው ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም እሱ ብቸኛ ነው ቃል ኪዳኑን ፈፀመ አገልግጋዩን (ሙሀመድን) ረዳ የተሰበሰበውን የጠላት ጦር ለብቻው ድል ነሳ) ዱዓውን ዚክሩን አንዴና ሁለቴ ብቻ ቢለውም ችግር የለውም እጅ የሚነሳው ለዱዓ ብቻ ነው። ተክቢራ በሚባልበት ወቅት እጅ አይነሳም። ከዚያ ከሰፋ ኮረብታ ውረድ በምትወርድበት ወቅት ለራስህ ለቤተሰብህና ለወገኖችህ የፈለግከውንና የቻልከውን ዱዓ እያደረግክ ወደ መርዋ አምራ በግራህና በቀኝህ በኩል አረንጓዴ ቀለም የተቀባው የግድግዳው ምሰሶ አጠገብ ስትደርስ ሌላኛው አረንጓዴ ምሰሶ አጠገብ እስክትደርሰ ድረስ መንገዱ ክፍት ከሆነልህ በደንብ እሩጥ። ሩጫው ወንዶችን እንጂ ሴቶችን አይመለከትም። ከአረንጋዴው ምሰሶ በኋላ ሩጫህን ሰመተው በእርምጃ ብቻ ጉዞህን ወደ መርዋ ቀጥል መርዋ በምትደርስበት ወቅት ፊትህን ወደ ካዕባ

በማዞር ሰፋ ላይ የሰራኸውን ሥራ በሙሉ ሥራ ። የቁርዓን አንቀፅ ግን አይደገምም ። በእንዲህ ዓይነቱ መልኩ ሰባት(7) ጊዜ በሁለቱ ኮረብታዎች መካከል ምልልስ አድርግ። ከሰፋ እስከ መርዋ ያደረግኸው ጉዞ እንደ አንድ ሰዕይ/ዙር/ ይቆጠራል፤ ከመርዋ ወደ ሰፋ መመለስህ ደግሞ እንደ ሁለተኛ ሰዕይ/ዙር/ ይቆጠራል ሰዕዩ (ምልልሱ) ሰፋ ተጀምሮ መርዋ ላይ ይጠናቀቃል። ለጠዋፉም ሆነ ለሰዕዩ የተለየና ግዴታ የሆነ ዚክር የለውም። ጠዋፍ ወይም ሰዕይ አድራጊው የቻለውን የፈለገውን ዱዓና ዚክር ያደርጋል ። ከፈለገ ቁርዓንም መቅራት ይችላል። ነገር ግን ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ያደረጓቸው ዱዓዎችና ዚክሮች ላይ ቢያተኩር ይመረጣል።

የሰዕይ ሥራህን ስታጠናቅቅ የራስ ፀጉርህን ተላጭ ወይም አሳጥር በነዚህ ሥራዎች አማካይነት የዑምራ ሥራህ

ይጠናቀቃል ። ከዚህ በኋላ በኢሕራም ምክንያት ተከልክለሃቸው የነበሩ ነገሮች በሙሉ ይፈቀዱልሃል ለምሳሌ መደበኛ ልብስ መልበስ ራስህን መሸፈን ጥፍር መቁረጥ ... ወዘተ። ምናልባት ያደረግከው ዑምራ የተመቱዕ ዑምራ ከሆነ ፀጉርህን ከመላጨት ማሳጠሩ ይሻላል ለምን ቢባል በሐጁ ጊዜ ስትፈታ መላጨቱ በላጭ ስለሚሆን ለመላጨት እንዲያመችህ ። ዑምራ አድራጊዋ ከሙሉ ፀጉሯ ጫፍ ላይ ወይንም ከአንዱ ጉንጉን ላይ የጣትዋን የላይኛውን ክፍል ያህል መቁረጥ ይኖርባታል እንጂ ሙሉ ፀጉሯን አትነካም

በጠዋፍና በሰዕይ መካከል ከቻልክ ዘምዘም ውሃ ብትጠጣ ተወዳጅ ነው ።

## የሐጅ ሥርዓት-አምልኮ አፈፃፀም

1. ሐጅ ብቻ አስበህ ወይም ሐጅንና ዑምራን በጣምራ ለመስራት አስበህ ከሆነ ለሐጅና ለዑምራ በምትመጣበት መንገድ ላይ ያለው

የኢሕራም ማድረጊያ ሥፍራ ላይ ኢሕራም አድርግ:: ምናልባት ኢሕራም ማድረጊያ ሥፍራውን ሳላውቀው ላልፈው እችላለሁ ወይም የሚነግረኝ ሰው የለም ብለህ ከሰጋህ አውሮኘላን ማረፊያው ውስጥ ሰግደህ ኢሕራም ማድረግ ትችላለህ ከፈለክም አውሮኘላኑ ውስጥ እንደገባህ ኢሕራም ማድረግ ትችላለህ ችግር የለውም ::

2.የመኖሪያ ሥፍራህ ከሚቃቱ (ከመነየቻ በታው) ውስጥ ማለትም ለመካ የቀረበ ከሆነ ባለህበት ሥፍራ ሆነህ ኢሕራም አድርግ

3.ሙተመቲዕ ከሆንክም በምትመጣበት መንገድ ላይ ያለው ሚቃት ላይ ለተመቱዕ ዑምራ የሚሆንህን ኢሕራም አድርግ የዑምራ ሥራህን ቀደም ሲል ባየነው የዑምራ አፈፃፀም ሂደት መሠረት ፈፅም ከዚያ እስከ ዙልሂጃህ ስምንተኛው(8) ዕለት ድረስ ነፃ ትሆናለህ ::

4. ዋነኞቹ የሐጅ ሥርዓተ ፀሎት ከንዋኔዎች የሚጀምሩት በዙልሂጃ ስምንተኛ ው (8) ቀን (የውሙተርዊየህ) ጀምሮ ነው ::

## የዙልሂጃ ስምንተኛው ዕለት (የውሙተርዊየህ)

በዚህ ዕለት ረፋድ ላይ ሙተመቲዕ የሆነ ሰው (ዑምራ አድርጎ እስከ ሐጅ ወቅት ተፈቶ የነበረው ሰው) ከዚህ ቀደም ለዑምራው ኢሕራም ከማድረጉ በፊት ያደረጋቸውን ነገሮች (ገላን መታጠብ ሰውነቱን ሽቶ መቀባትና ሰላት መስገድ... ወዘተ) በማድረግ ለሐጁ ካለበት ሥፍራ ሆኖ ኢሕራም ያደርጋል::

ቃሪን (ሐጅንና ዑምራን በአንድ ያቆራኘ) ና ሙፍሪድ (ለሐጅ ብቻ ኢሕራም ያደረገ) ከጅምሩ ጀምሮ በኢሕራም ላይ ስለኾኑ ድጋሚ ለሐጅ ኢሕራም ማድረግ አያስፈልጋቸውም::

«ሙፈሪዱም» «ቃሪኑም» «ሙተመቲዑም» ከቀትር በፊት ሁላቸውም ወደ ሚና ይጓዛሉ:: ዙህርን፣ ዐስርን፣ መግሪብንና፣ ዒሻን ሚና ላይ ይሰግዳሉ:: አስጋገዱም እያንዳንዱን ሰላት በወቅቱ መስገድ ሲሆን «ጀምዕ» ማድረግ(ሁለት ሰላቶችን በአንድ ማጣመር) ግን የለባቸውም:: በዕለቱ ባለአራት ረከዓ ሰላቶቹን ብቻ ሁለት ሁለት ረከዓ እያደረጉ በወቅቱ ይሰግዳሉ:: የዙልሂጃን ዘጠነኛ ሌሊት ሚና ያድራሉ:: የሱብሂን ሰላት እዚያው ሚና ይሰግዳሉ:: ከስምንተኛው(8) ቀን በፊት ቀደም ብሎ ሚና የደረሰ ሰው ካለ ለሐጅ ኢሕራም ካላደረገ ረፋድ ወቅት ላይ እዚያው ሚና ላይ ሆኖ ኢሕራም ያደርጋል:: ዘጠነኛ ውን ቀን ሱብሂ ሚና ላይ ከሰገዱ በኋላ ፀሀይ እስክትወጣ ድረስ ቆይቶ ፀሀይ ከወጣች በኋላ አላህን በፈለጉት ዚክር እያወደሱት ተልቢያ እያሉና ቁርዓን እየቀሩ በእርጋታና በዝግታ ወደ አረፋ ማቅናት/ማምራት/:: ተልቢያ ላኢላሀኢልለሏህ አልሏሁ አክበርንና

አልሀምዱሊላሂን ከምን ጊዜውም በበለጠ ማብዛት ተወዳጅ ነው።

## የዙልሂጃ ዘጠነኛው ዕለት (የውሙ ዐረፋ)

የአረፋ ዕለት (የዙልሂጃ ዘጠነኛው ቀን) ዐረፋ ምድር ላይ መገኘት ከሐጅ ማዕዘናት አንዱ ሲሆን ያለርሱ ሐጁ በምንም ዓይነት መልኩ የተሟላ ሊሆን አይችልም ምክንያቱም ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ሲናገሩ «ሐጅ ማለት አረፋ ላይ መገኘት ነው» ብለዋልና::

## የዐረፋ ዕለት

ፀሀይ ከወጣችባቸው ዕለታት ሁሉ አላህ ዘንድ በላጭ ዕለት ነው:: ፀሀይ ከወጣችበት ጀምሮ እስክትጠልቅ ድረስ ሁሉም ሐጃጆች በአረፋ ሜዳ ላይ ለመገኘት የሚመጡበትና ፈጣሪያቸውን አላህን የሚማፀኑበት አላህም በዚህ ስብሰባቸውና ተግባራቸው መላዕክቶችን የሚፎካከርበትና የሚያስቀናበት ዕለት ነው::

በሶሂህ ሙስሊም ዘገባ ውስጥ እናታችን ዓኢሻ(ረ.ዐ) ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) «አላህ የሰው

ልጆችን ከእሳት ነፃ ከሚያወጣባቸው ዕለታት ሁሉ እንደ ዐረፋ ዕለት እጅግ በርካታ ሰዎችን ከእሳት ነፃ የሚያደርግበት ዕለት የለም በዕለቱ አላህ እራሱ አረፋ ሜዳ ወደቆሙት ሰዎች ጠጋ በማለት በነርሱ መላዕክትን ያስቀናበታል። እነዚህ አገልጋዬቼ ዛሬ እዚህ ሥፍራ ላይ የተሰበሰቡት ከኔ ምን ፈልገው ነው? እያለ መላዕክቶቹን ይጠይቃል።» ብለው መናገራቸውን ገልፀዋል።

## በዕለተ ዐረፋ ልናከናውናቸው የሚገቡ ነገሮች

- ከቻልን የዙህር ወቅት እስኪገባ ድረስ «ነሚራ» ተብሎ የሚጠራው ሥፍራ (በአሁኑ ወቅት መስጊድ ተሰርቶበታል) ላይ መቆየት ተወዳጅ ሱንና ነው። ምክንያቱም ይህ ሥፍራ ነብያችን(ሰ.ዐ.ወ) በመሰናበቻው ሐጃቸው ላይ የቆዩበት ሥፍራ ነበርና። የነሚራ መስጂድ ግማሹ ክፍል ዐረፋ ምድር ላይ ሲሆን ቀሪው ክፍል ደግሞ ከዐረፋ ክልል

ውጪ ነው ስለዚህ ከሰላት በኋላ ጀምበር እስክትጠልቅ ድረስ እዚያው መስጂዱ ውስጥ መቆየትን የሚመርጡ ሰዎች ካሉ በዐረፋ ክልል ላይ የሚገኘው የመስጂድ አካል ላይ መሆናቸውን በሚገባ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል::

- የዙህር ወቅት ሲገባ ኢማሙ(ኹጥባ) ካሰሙ በኋላ ዙህርንና ዐስርን በማሳጠር አንድ ላይ (ጀምዕ) አድርገው ያሰግዳሉ:: የሚደረገው አዛን አንድ ሲሆን ኢቃሙ ግን ሁለት ነው የሚሆነው:: ይህም ልክ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) እንዳደረጉት ማለትነው ::

- ከፈርድ ሰላቶች በፊትም ሆነ መካከል እንዲሁም በኋላ ምንም ዓይነት ሰላት አይሰገድም

ሐጃጁ ሰላቱን ጀምዕ/አንድ ላይ/ አድርጐ ከሰገደ በኋላ በዐረፋ ክልል ውስጥ መሆኑን በሚገባ ማረጋገጥ ይኖርበታል :: ዙህርንና

ዐስርን ጀምዕ አድርገን ከሰገድን በኋላ ፀሐይ እስክትገባ ድረስ ዱዓና ዚክር በማድረግ ላይ እጅግ ልንበረታ ይገባል እንደ አንዳንድ አላዋቂዎች በአልባሌ ወሬና በከንቱ ሥራ ይህን ብርቅዬ አጋጣሚ ልናጠፋው አይገባም:: በተለይ በተለይ በዚህ በተባረከ ዕለትና በተቀደሰ ሥፍራ ድካማችንን ከንቱ ከሚያደርግና ምንዳችንን ሊያጠፋ ከሚችል ማንኛውም ጥፋት(ወንጀል) እጅግ መጠንቀቅ ይኖርብናል ::

### በዕለተ ዐረፋ የሚፈፀሙ ስህተቶች

በዐረፋ ዕለት በርካታ ሐጃጆች የተለያዩ ስህተቶች ላይ ሲወድቁ ይታያሉ ::

ከነዚህም ስህተቶች ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል

1. ከዐረፋ ክልል ውጭ መሆንና ጀምበር እስክትጠልቅ ድረስ እዚያው መቆየት ከዚያ ወደ ሙዝደሊፋ መመለስ ይህንን ተግባር

የፈፀመ ሰው ሐጅ አላደረገምና ሐጅ የለውም ::

2. ጀምበር ከመጥለቋ በፊት የአረፋን ክልል ለቆ መውጣት ይህን ድርጊት መፈጸም ፍፁም የተከለከለ ነው:: ምክንያቱም የነብዩን(ሰ.ዐ.ወ) መመሪያ መጣስ ነውና ::

3. ዐረፋ ተራራ ላይ ለመውጣትና ጫፉ ላይ ለመድረስ ብሎ መጋፋትና መጨናነቅ፣ በተራራው በረካ ለማግኘት በሚል መተሻሸትና እሱን ነክቶ ፊትንና ሰውነትን ማበስ፣ ተራራው ጫፍ ላይ ወይም ሌላ ክፍሉ ላይ ሆኖ መስገድ ... ወዘተ ይህ ድርጊት ከኢስላም ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው የፈጠራ ድርጊት ነው:: ምንም ዓይነት በረካም ሆነ አጅር ከአላህ ዘንድ አያስገኝም እንዲያውም በወንጀለኛነት አላህ ዘንድ ያስጠይቃል:: ከዚህም ባሻገር ከፍተኛ የጤናና የአካል ጉዳት በሰዎች ላይ እንዲደርስ መንስኤ እየሆነ ይገኛልና ጠንቀቅ ማለት ነው ::

4. ሌላው ደግሞ አረፋ ላይ ጎልቶ የሚታየው ስህተት ወደ አረፋ ተራራ ፊትን አዙሮ ዱዓ ማድረግ ነው። በመሰረቱ ዱዓ በምናደርግበት ወቅት ፊታችንን ማዞር ያለብን ወደ ቂብላ ነው እንጂ ወደ ተራራው አይደለም ።

## ሙዝደሊፋ

ዘጠነኛው ቀን ላይ(የዐረፋ ዕለት) ጀምበር ስትጠልቅ ሐጃጆቹ ለዚህ ለተባረከ ቀይታ አረፋ ምድር ላይ ለመገኘት ላበቃቸው አምላክ ምስጋና እያቀረቡ ተልብያ እያሉና አላህን እየዘከሩ ሙዝደሊፋ ላይ ሌሊቱን ለማደር ጉዞአቸውን ወደ እዚያው ያደርጋሉ ። ሙዝደሊፋ እንደደረሱ ወዲያው መግሪብና ዒሻን በአንድ አዛን በሁለት ኢቃም አንድ ላይ አድርገው በማሳጠር ይሰግዳሉ። አንዳንድ ሐጃጆች ሙዝደሊፋ እንደ ደረሱ አላስፈላጊ ተግባሮች ላይ ይሰማራሉ እንዲሁም አንዳንድ ስህተቶችን ይፈጽማሉ ። ከነዚህ ስህተቶች

እስቲ አንዳንዶቹን ለግንዛቤ ያህል እንመልከት :-

ሀ. የመግሪብና የዒሻን ሰላት ከመስገዳቸው በፊት ጠጠር ለቀማ ላይ መሰማራት
ለ. ጠጠሮቹን ከሰበሰቡ በኋላ ውሃ ፈልገው ማጠብ እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ከነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም ::
ሐ. ጀመራቶቹን (የጠጠር መወርወሪያ ገንዳዎቹን) ከሙዝደሊፋ በተለቀሙ ጠጠሮች እንጂ ከሌላ ቦታ በተለቀሙ ጠጠሮች መወርወር አይቻልም የሚል የተሳሳተ ከንቱ አቋም መያዝና ከሙዝደሊፋ ለሁሉም ቀናቶች መወርወሪያ የሚሆኑ ጠጠሮችን ተሸክሞ ወደ ሚና መምጣትና ሌሎችም ይጠቀሳሉ ::

በዕለቱ ሱናው ከላይ እንደጠቀስነው ሐጃጆቹ ሌሊቱን በሙሉ ሙዝደሊፋ በማደር የሱብሂን ሰላት ሙዝደሊፋ መስገድ ነው ::

ነገር ግን ሴቶች ህፃናቶች አካል ጉዳተኞች ደካማ አዛውንቶችና እነሱን የሚንከባከቡ ወገኖች ከእኩሉ ሌሊት በኋላ ወደ ሚና መንቀሳቀስ ይፈቀድላቸዋል ። ሚና እንደደረሱ ጠጠራቸውን ይወረውራሉ ።

ሐጃጁ በሙዝደሊፋ ላይ የሱብሂን ሰላት ከሰገደ በኋላ መሽዐረል ሀራም(ሙዝደሊፋ ውስጥ ያለተራራ ነው) አጠገብ ወይም ሙዝደሊፋ ውስጥ ማንኛውም ሥፍራ ላይ በመሆን ፊቱን ወደ ቂብላ አዙሮ የፈለገውን ዱዓና ዚክር እንዲሁም ተክቢራ እያደረገ ይቆያል ። ከዚያ ፀሀይ ለመውጣት ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሯት ወደ ሚና ጉዞ ይጀምራል። በጉዞው ላይ እያለ ከሙዝደሊፋ ክልልም ሆነ ከሌላ ሥፍራ ከሽምብራ ትንሽ ከፍ ያሉ ሰባት ጠጠሮችን ጀምረተል ዐቀባ(ጀምረተል ኩብራ) ላይ ለመወርወር ይለቅማል። በሌሎች ቀናቶች የሚወረወሩትን ጠጠሮች ግን የሚለቀመው ከሚና ነው።

ከዚያ ተልቢያ እያለ ዚክር በብዛት እየዘከረ ለአላህ ተናንሶ በአላህ በረከት ጉዞውን ወደ ሚና ያደርጋል ። ሚና እንደደረሰ ጊዜ ሳያጠፋ በቀጥታ ወደ ጀምረተል ኩብራ ያመራል ። «ጀምረተል ኩብራ» ማለት ለመካ ከተማ ቀረብ ያለው የጠጠር መወርወሪያ ሥፍራ ነው ። ሥፍራው ሲደርስ ተልቢያ ማለቱን ያቆማል። ከዚያ የሚከተሉትን ተግባሮች በቅደም ተከተሉ መሠረት ይፈፅማል ቅደም ተከተሉ ቢዛባም ችግር የለውም ግን ሱናው(በላጩ) በቅደም ተከተሉ መሠረት መሥራት ነው ።

1. ከእያንዳንዱ ጠጠር ጋር ተክቢራ (አልኳሁ አክበር) እያለ ሰባት ጠጠሮችን በተከታታይ ጀምረተል ዐቀባ (ጀምረተል ኩብራ) ላይ ይወረውራል ።
2. ሀድይ(ዕርድ) ካለበት ከቻለ እርዱን ያርዳል ከእርዱም ላይ ይበላል ለችግረኞችም ያበላል የማይቻል ከሆነ ገንዘቡን

ለሚያርዱለት ወገኖች ቀደም ብሎ መካ እያለ ይሰጣል ወይም ለባንክ ይከፍላል ።

3. ፀጉሩን ያሳጥራል ወይም ይላጫል መላጨቱ በላጭ ነው። ሐጃጂ ከፀጉራ ጉንጉን ከአንዱ ወይም ከፈለገች ከሙሉ ፀጉራ ላይ የአንድ ጧቷን ጫፍ ያህል ትቆርጣለች ።

4. ሐጃጁ እነዚህን ሥራዎች በአግባቡ ካከናወነ በኋላ ወደ መስጂደል ሀረም ጠዋፈል ኢፏዳ ለማድረግ ይጓዛል ።

## የዙልሒጃ አሥረኛ ቀን

ይህ ዕለት የውሙንነህር (የማረጃው ዕለት)በመባል ይታወቃል ይህ እለት የዒድ አል-አድሀ በዓላት ቀናት የመጀመሪያው ዕለት ነው ። ይህ ዕለት በዓለም ላይ ያሉ መስሊሞች ሁሉ በድምቀት የሚቀበሉት ሐጃጆች ደግሞ በሚና ምድር ላይ ሆነው ፍፁም በተለየ መልኩ የሚያከብሩት የተባረከና የተቀደሰ ዕለት ነው ። ዕለቱ ሙስሊሞች ወደ አላህ ለመቃረብ ብለው ኡዱሂያቸውን (ዕርዳቸውን) አርደው በአላህ ፀጋ ተደስተው የሚውሉበት በዕለቱ ሐጃጆች ጠጠራቸውን ከወረወሩበት ጊዜ ጀምሮ «አልሏሁአክበር አልሏሁአክበርወሊላሂልሐምድ» እያሉ ተክቢራቸውን ማስተጋባት የሚጀምሩበት ታላቅ ቀን ነው ።

እዚህ ላይ እንደ ማሳሰቢያ ማንሳት የምንወደው ነገር ቢኖር አንዳንድ ሐጃጆች

ጠጠር በሚወረውሩበት ወቅት የሚፈፅሟቸውን ስህተቶችን ነው ።

ሀ. አንዳንድ ሐጃጆች ጠጠር መወርወሪያው ላይ ጠጠር ሲወረውሩ በጠጠሩ ሰይጣንን የሚወግሩ እየመሰላቸው በቁጣ ተሞልተው ሰይጣንን በመስደብና በመርገም ጠጠሩን ሲወረውሩ ይታያል ። ይህ ጠጠር ውርወራ በእውነቱ አላህን ለማስታወስና ለመታዘዝ እንጂ ሰይጣናትን ለመውገርና ለመሳደብ ተብሎ የተደነገገ አይደለም ።

ለ. የጠጠር መወርወሪያዎች ሥፍራ ላይ ትልልቅ ድንጋዬችን ጫማዎችንና እንጨቶችን መወርወር ይህ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በሀዲሳቸው ያወገዙት በሃይማኖት(በዲን ላይ ወሰን ማለፍ (ጉሉው) ነው ።

ሐ. ጠጠር መወርወሪያዎቹ ሥፍራ ላይ ጠጠር ለመወርወር ብሎ መፊፋትና መጣላት ትልቅ ስህተት ነው ማንኛውም ሐጃጅ ለቋስሊም ወንድሞቹና እህቶቹ ከማንም የበለጠ ሊራራላቸውና ሊያዝንላቸው ይገባል ::ሐጃጁ በሚወረውርበት ወቅት ጠጠሩ ገንዳው ውስጥ ትክክለኛ ሥፍራው ላይ ማረፉን እንጂ ምሰሶውን ስለመምታት አለመምታቱ ሊጨነቅ አይገባም ::

መ. ሁሉንም ጠጠር በአንድ ላይ መወርወር በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ጠጠሩን ከወረወረ ሰባቱ ጠጠርእንደ አንድ ጠጠር ነው የሚታሰበው ስለዚህ እያንዳንዱን ጠጠር ተራ በተራ ከተክቢራ (አልሏሁ አክበር) ጋርነው መወርወር ያቀበት ሐጃጁ ጀምረተል ዐቀባ(ጀምረተል ኩብራ) ላይ ከወረወረ ፀጉሩን ከላጨ ወይም ካሳጠረ የመጀመሪያውን መፈታት (ተሐሉለል አወልን)ተፈቷል :: ከዚህ በኋላ ከግብረ ሥጋ-ግንኙት ውጭ ያሉ

ማንኛውም በኢህራሙ አማ ካይነት ተከልክሏቸው የነበሩ ነገሮች ሁሉ ይፈቀዱለታል ::

## የጠጠር አወራወር ሥርዓት

1. የዒድ ዕለት/10ኛው ቀን ከላይ/ እንደተጠቀሰው ከሙዝደሊፋ ተመቂሰህ ሚና ስትደርስ ሰባት ጠጠሮችን በመያዝ ወደ ጀምረተል ኩብራ(አቀባ) በማምራት ጠጠር መወርወሪያው ስፍራ ላይ ከእያንዳንዱ ጠጠር ጋር ተክቢራ እያልክ ትወረውራለህ :: በዚህ ዕለት ከዚህ መወርወሪያ ስፍራ ውጪ ሌሎች የጠጠር መወርወሪያዎች ላይ አይወረወርም ::

2. በሶስቱ ቀናቶች (በአያመት- ተሽሪቅ) ሶስቱም የጠጠር መወርወሪያ ሥፍራዎች ላይ ወርውር :: እያንዳንዳቸው ላይ ሰባት ሰባት ጠጠር ትወረውራለህ ከእያንዳንዱ ጠጠር ጋር «አልሏሁአክበር» እያልክ መወርወርህን አትዘንጋ::

የመወርወሪያ ስፍራዎቹ 1ኛ «ጀምረቱስሱግራ» 2ኛ«ጀምረቱል ውስጧ»«ጀምረቱል ኩብራ (አቀባ)» ሲሆኑ በአያመት-ተሽሪቅ ላይ ስንወረውር ከጀምረቱስ ሱግራ ጀምረን ጀምረተል ኩብራ/አቀባ/ ላይ እናበቃለን::

በሶስቱ ቀናት /አያመትተሽሪቅ / ጠጠር የሚወረወረው የዙሁር ወቅት ከገባበት ጀምሮ እስከ ምሽት ድረስ ባለው ወቅት ነው ::

## ጠዋፈል ኢፋዳ

«ጠዋፈል ኢፋዳ» ከሐጅ ማዕዘናት አንዱ ማዕዘን ሲሆን ያለ እሱ ሐጅ ሊሟላ አይችልም :: የዒድ ዕለት /10ኛው ዙልሂጃ/ ጠዋት ሐጃጁ ጀምረተል ዐቀባ ላይ ጠጠር ከወረወረና ፀጉሩን ከላጨ በኋላ እንዲሁም ማረድ ከቻለ አርዶ ወደ መ ኻ በመሄድ «ጠዋፋል ኢፋዳ» ያደርጋል :: ጠዋፋ እንደ

መጀመሪያው ጠዋፍ ሰባት/7/ ዙር ሲሆን ነገር ግን እዚህ ጠዋፍ ላይ ትከሻ መግለጽም ሆነ ሮጥ ሮጥ ማለት የለም ። ጠዋፉን ሲጨርስ ሙተመቲዕ ከሆነ አልያም ደግሞ «ቃሪን ወይም ሙፍሪድ ሆኖ ከመግቢያ ጠዋፍ /ጠዋፈልቁደም/ ጋር» ሰዕይ» ካላደረገ» ሰዕይ» የማድረግ ግዴታ አለበት ። አደራረጉም ቀደም ሲል እንዳየነው በሰፋና መርዋ መካከል ሰባት ምልልስ ማድረግ ነው ። ጠዋፈል ኢፋዷን በእለቱ ማድረግ ካልተቻለ እስከ መጪዎች ሶስት ቀናት ድረስ ማቆየት ይቻላል ። በዕለቱ ማድረጉ ግን በላጭ ነው ። ጠዋፈል ኢፋዷ ሳያደርግ ሶስቱን የአያመትተሽሪቅ ቀናት ሚና ቆይቶ ጠጠር ወርውሮ ወደ መ ካ ሲመለስ ማድረግም ይቻላል ። «ጠዋፈል ኢፋዷን ካደረገ በኢሕራም አማካይነት ተከልክሏቸው የነበሩ ነገሮች በሙሉ ይፈቀዱለታል ። ይህም ማለት የግብረሥጋ-ግንኙነት ማድረግን

ጨምሮ ማለት ነው ። ፍቺው «ተሐሉለስሳኒ» በመባል ይታወቃል ።

## አያሙትተሽሪቅ

«አያሙትተሽሪቅ»ተብለው የሚጠሩት ቀናት የሚጀምሩት ከ11ኛው ዙልሂጃ ሌሊት ጀምሮ ሲሆን የሚያበቁት ደግሞ በዙልሂጃ 13ኛው ቀን ከቀትር በኋላ ይሆናል ። ሐጃጁ በዒድ ቀን ( አስረኛው ዙልሂጃ ) ጠዋፈል ኢፋዳን ከአደረገ በኋላ ሶስቱን የአያመት ተሽሪቅ ሌሊቶች ሚና ለማደር ወደ ሚና መመለስ ይኖርበታል። ወይም ደግሞ ቸኩሎ ከሆነ ቢያንስ ሁለቱን ሌሊቶች ለማደር ወደ ሚና የመመለስ ግዴታ አለበት ።

እያንዳንዱ ሐጃጅ በነዚህ ቀናቶች ውስጥ ቀጥለው የሚጠቀሱትን ነገሮች ማስተዋል ይኖርበታል ።

ሀ. ሚና በሚያድርባቸው ቀናቶች ውስጥ ጠጠር መወርወር ያለበት ከቀትር በኋላ መሆኑን

ለ. ከእያንዳንዱ ጠጠር ጋር ተክቢራ (አላሁአክበር) ማለቱን

ሐ. ዱዓና ዚክር ማብዛቱን

መ. እርጋታና ስክነት መላበሱን

ሠ መጋፋት ፣መጨቃጨቅ፣ ቂም መያዝን መራቁን ... ወዘተ ::

ማንኛውም ሐጃጅ «ጀምረተ-ስሱግራ» ና«ጀምረተል ውስጧ» ላይ ጠጠር ከወረወረ በኋላ ይህም ማለት እያንዳንዱ ጠጠር መወርወሪያ ገንዳ ውስጥ ጠጠሮቹን ከወረወረ በኋላ ወደ ቀኙ ፈንጠር ብሎ ቆሞ ፊቱን ወደ ቂብላ አዙሮ ሁለት እጆቹን ከፍ አድርጐ የፈለገውን ዱዓ ማድረግ ሱና ነው :: ጀምረተል አቀባን (3ኛውን) ከወረወረ በኋላ ግን መቆምና ዱዓ ማድረግ ሱና አይደለም::

በቀጥታ ወደ መጣበት መመለስ (መሄድ)ብቻ ነው የሚኖርበት ::

- በሁለቱ የእያመት ተሽሪቅ  ቀናት ውስጥ ስራውን አጠናቆ ቶሎ ወደ አገሩ ለመመለስ የቸኮለ ሰው በ12ኛ ቀን ላይ ከዙሁር በኋላ ሶስቱንም ጀመራቶች ወርውሮ ጀምበር ከመጥለቋ በፊት  የሚናን ምድር ለቆ መውጣት ይኖርበታል :: ሚና እያለ ጀምበር ከጠለቀችበት ግን 13ኛውን ሌሊት ሚና የማደርና እንዲሁም 13ኛው ቀን ላይ ሶስቱም ስፍራዎች ላይ ጠጠር የመወርወር ግዴታ አለበት:: ይህ የማደር ግዴታ የሚፀናው ሐጃጅ ለጉዞ ቸኩሎ ተነስቶ ነገር ግን መሰናዶውን በሚገባ ያላጠናቀቀ እንደሆነ ብቻ ነው :: መሰናዶውን በሚገባ አጠናቆ ለመውጣት ቸኩሎ እያለ በድንገት ጀምበር ጠልቃበት ከሆነ ግን እንዲያድር አይገደድም ::

## ጠዋፈል ወዳዕ ( የመሰናበቻ ጠዋፍ)

ሐጃጆቹ ከሚና የሐጅ ሥራቸውን አጠናቅቀው ከወጡ በኋላ ወደ አገራቸው ለመመለስ ዝግጅታቸውን ሲያጠናቅቁ የመካን ምድር ከመልቀቃቸው በፊት ወደ ተከበረው የአላህ ቤት (ካዕባ) በመምጣት «ጠዋፈልወዳዕ» (የመሰናበቻ ጠዋፍ) ያደርጋሉ ። ሐጃጆች ይህን የመሰናበቻ ጠዋፍ የሚያደርጉት «ማንኛውም ሐጃጅ የመካን ምድር ለቆ በሚወጣበት ወቅት የመጨረሻ ስንብቱ ካዕባ ላይ ሳይሆን እንዳይሄድ» ብለው የተናገሩትን የረሱልን (ሰ.ዐ.ወ) ትዕዛዝ ለመፈፀም ብለው ነው ።

ጠዋፈል ወዳዕ ከሐጅ ግዴታዎች የመጨረሻው ግዴታ/ዋጅብ / ነው ። ስለዚህ ማንኛውም ሐጃጅ ወደ አገሩ ለመሄድ ሲነሳ ጠዋፈል ወዳዕ የማድረግ ግዴታ አለበት ። ይህ ግዴታ የሚነሳላቸው በወር አበባና በወሊድ ደም ላይ ያሉ ሴቶች ብቻ ናቸው ።

ምክንያቱም ለጠዋፍ እንደ ሰላት ሁሉ ጡሃራ መሆንና ውዱዕ ማድረግ ሸርጥ ነውና ፡፡

## ተጨማሪ ማስታወሻዎች

- ማንኛውም ጠዋፍ አድራጊ መስጂዱ ውስጥ ምድር ላይ ቦታ ካላገኘ መስጂዱ ፎቅ ላይ ሆኖ ጠዋፍ ማድረግ እንደሚችል በርካታ ኡለማዎች ፈትዋ ሰጥተውበታል ፡፡
- የዐረፋ ምድር ሁሉ በዓረፋ ዕለት ለመቆያነት ስለሚያገለግል የግድ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) የቆሙበት ቦታ ካልሆነ ብሎ እራስን ለችግር መዳረግ ተገቢ አይደለምና በተገኘው ቦታ መቆም
- በርካታ ዑለማዎች በመስጂደል ሀረም በሚሰግድ ሰው ፊትለፊት ሱትራ ባይኖርም እንኳን ማቋረጥ ችግር የለውም ይፈቀዳል ብለዋል፡፡
- ጠዋፍ በሒጅሩ ኢስማኢል ውስጥ አቋርጦ ማድረግ አይፈቀድም ምክንያቱም ይህ ስፍራ የቤቱ አካል ነውና ፡፡

## የታላቁ የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ ጉብኝት ሥርዓት

የነብያችን(ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ መጎብኘት በመሠረቱ ከሐጅ ሥራ ጋር የሚያገናኘው ነገር ፈጽሞ የለም:: የሐጅ ሸርጥም አይደለም ለሐጁ አካልም አይደለም:: እንዲሁም አንዳንድ ሰዎች እንደሚያስቡት ዚያራው በራሱ ዋጂብም አይደለም:: ነገር ግን ማንኛውም ሙስሊም በዓመት ውስጥ በየትኛውም ጊዜ አቅሙ ከፈቀደለት የነብያችንን(ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ መዘየሩ ተወዳጅ ኢባዳ(ሱና) ነው:: በተለይ ደግሞ አላህ በሐጅ አማካይነትም ይሁን በሌላ ሁለቱን ቅዱሳን ከተሞች (መካና መዲና) ለመዘየር ዕድሉን ከሰጠው እግረመንገዱን የረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ ሰላት ለመስገድ ብሎ ቢዘይር ከዚያም ወደ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ቀብር ጠጋ ብሎ ለነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ሰላምታ ቢያቀርብ ሱና ነው :: በነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ የሚሰገድ

ሰላት ሌላ መስጂድ ከሚሰገድ ሰላት በአንድ ሺህ እጥፍ ይበልጣል:: ይህ ብልጫ መስጂደል ሐራምን አይመለከትም ምክንያቱም መስጂደል ሐራም የሚሰገደው ሰላት ሌሎች መስጊዶች ከሚሰገደው ሰላት በመቶ ሺ (100.000) እጥፍ ይበልጣልና :: ጉብኚው መስጂደን ነበዊይ (የነብዩ መስጂድ) እንደደረሰ

بسم الله والصلاة والسلام على رسول الله أعوذ بالله العظيم ووجهه الكريم وسلطانه القديم من الشيطان الرجيم اللهم افتح لى أبواب رحمتك.

«ቢስሚላሂ ወስሰላቱ ወስሰላሙ ዓላ ረሡሊሏህ አኡዙቢላሂልዐዚም ወወጂሂ ሂልከሪም ወሡልጣኒሂል ቀዲም ሚነሽይጣንኒረጂም አላሁም መፍተህሊ አብዋበ ረህመቲከ» (በአላህ ስም ውዳሴና ሠላም በአላህመልዕክተኛ ላይ ይሁን በሃያሉ አላህ በተከበረው ፊቱ በዘላለማዊ ስልጣኑ ከተረገመው ሰይጣን እጠበቃለሁ አላህ ሆይ! የዕዝነት በሮችህን ክፈትልኝ) በማለት የቀኝ

እግሩን በማስቀደም ወደ መስጂዱ ይገባል ፡፡ ይህ ዱዓ ሌሎች መስጊዶች በምንገባበት ወቅትም ያገለግላል፡፡ ጉብኝው መስጂደን ነበዊይ ከገባ በኋላ ሌላ ስራዎች ውስጥ ከመግባቱ በፊት ተህየተል መስጂድ ሁለት ረከዓ ይሰግዳል፡፡ ከቻለ ረውዳው( በሚንበሩና በእናታችን ዓኢሻ(ረ.ዐ) ቤት መካከል ያለ ስፈራ ነው ) ላይ ቢሰግድ ተወጃጅ ነው ካልቻለ መስጂዱ ውስጥ የትኛውም ስፍራ ላይ ቢሰግድ ችግር የለውም ከዚያ ወደ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ቀብር በመሄድ መቃብሩን ተጠግቶ ፊት ለፊት በመቆም በአደብ ድምፁን ዝቅ አድርጐ

السلام عليك أيها النبي ورحمة الله وبركاته

«አስሰላሙ ዓለይከ አዩሀን ነብዩ ወራህመቱልላሂ ወበረካቱሁ» (አንተነብዩ ሆይ! የአላህ ሰላም እዝነትና በረከት ባንተ ላይ ይሁን) በማለት ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰላምታን ያቀርባል፡፡ በሳቸው ላይ ሰለዋትም ያደርጋል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከፈለገ

اللـهم أته الوسيلة والفضيلة وابعثه المقام المحمود الذى وعدته اللهم اجزه عن أمته افضل الجزاء.

«አላሁመ አቲሂልወሲለተ ወልፈዲለተ ወብዐስሁል መቃመልመሕሙደልለዚወአድተሁ አልኋሁመጅዚሂ ዐን ዑመቲሂ አፍደለል ጀዛዕ»(አላህ ሆይ! ለነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አልወሲላንና (ጀነት ላይ ያለች ልዩ ሥፍራ ናት) ከሌሎች ሰዎች ሁሉ የላቀን ደረጃ ስጣቸው ቃል የገባህላቸውን ምስጉን ስፍራ አድርሳቸው አላህ ሆይ! ለህዝባቸው ለዋሉት ውለታ የላቀን ምንዳ ስጣቸው) ቢልም ጥሩ ነው ::

የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ)ቀብር ከዘየረ በኋላ ትንሽ ወደ ቀኝ ፈቅ በማለት የአቡበከር ሲዲቅ(ረ.ዐ) መቃብር ፊትለፊት በመቆም በአቡበከር ላይ ሰላምታ ያቀርባል:: ለሳቸውም አላህ እዝነቱን ምህረቱንና ውዴታውን እንዲቸራቸው ዱዓ የደርጋል :: ከዚያ አሁንም በድጋሚ ወደቀኝ

ትንሽ ፈቅ በማለት የኡመር(ረ.ዐ) መቃብር ፊትለፊት በመቆም በኡመር ላይ ሰላምታ ያቀርባል፡፡ ለእሳቸውም አላህ እዝነቱንና ፍቅሩን እንዲለግሳቸው አላህን ይለምናል ፡፡

አንዳንድ ጉብኝዎች የነብዩን(ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ በሚገበኙበት ወቅት መሠረተቢስ የሆኑ ከሰሃባዎች ያልተገኙ ተግባሮችን በመፈጸም ስህተት ላይ ሲወድቁ ይስተዋላል ፡፡

***ለምሳሌ***፡- የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መቃብር የሚገኝበትን ቤት መስኮት በርና ግድግዳ በእጅ በመንካት ፊትንና ሰውነትን ማባበስ የመስጂዱን ግድግዳዎች መሳም መሳለም .. ወዘተ፡፡ ይህ ፍፁም ስህተት ነው፡፡

ሌላው በዱዓ ወቅት ቀብሩን መቅጣጨት(ፊትን ወደ ቀብሩ አዙሮ መለመን) ሲሆን ይህም እንዲሁ ስህተት

ነው ። በዱዓ ወቅት ተገቢና መሆን ያለበት ፊታችን ወደ ቂብላ ማዞር ነው ።
የረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ ለሚጎበኝ ሰው እግረመንገዱን የሚከተሉትን ተግባራቶች ቢፈፅም ይወደድለታል ።
1/ ዑስማን ኢብኑ ዐፋን(ረ.ዐ)ና ሌሎችም በርካታ ሰሀባዎች የተቀበሩበትን የበቂዕ መካነ-መቃብር መዘየርና ለሙታኖቹ ዱዓ ማድረግ
2/ የሰማዕታት ቁንጮ የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) አጎት የሆኑትን ሀምዛንና ሌሎችን በርካታ የእሁድ ሸሂዶችን አቅፎ የያዘውን የእሁድ መካነ መቃብርን በመዘየር ለሰማዕታቱ (ለሸሂዶቹ) ነብዩ ባስተማሩት መልክ ሠላምታ ማቅረብና ዱዓ ማድረግ ። ሠላምታና ዱዓ አደራረጉ እንደሚከተለው ነው ።

السلام عليكم أهل الديار من المؤ منين والمسلمين وأنا
إن شاء الله بكم لا حقون نسال الله لنا ولكم العافية

«አስሰላሙ ዓለይኩምአህሉድዲያር ሚነል ሙዕሚኒን ወል ሙስሊሚን ወኢንና

ኢንሻአልሏሁ ቢኩም ላሒቁን ነስአሉልሏሀ ለና ወለኩሙልዓፊያሀ»
(ከሙዕሚኖችና ከመስሊሞች የሆናችሁ የዚህ አገር ሰዎች(የመቃብሩን ሰዎችን ነው) ሰላም በናንተ ላይ ይሁን እኛ እዚህ ሥፍራ ላይ አላህ ካለ እናንተን እንከተላለን ለኛም ለናንተም አላህ ሠላሙን ጤናውን እንዲሰጠን እንማፀነዋለን ።)

3/ በኢስላም ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደተገነባው የቁባዕ መስጂድ ውዱዕ አድርጎ በመሄድ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንደፈፀሙት ተህየተል መስጂድ መስገድ

ከላይ ከተጠቀሱት ዚያራዎች ውጭ በመዲና ከተማ ውስጥ ሌሎች አጅር የሚያስገኙና ሱና የሚሆኑ የዚያራ ስፍራዎች የሉም። ስለዚህ ከነዚህ ቦታዎች ውጭ ሌሎችን ቦታዎች እንዘይራለን ብለን

ጊዜያችንን ጉልበታችንንና ገንዘባችንን ፋይዳ ቢስ በሆነ ነገር ማባከን ተገቢ አይደለም ።

## ማጠቃለያ

ሐጅ ሦስት ዓይነት የአፈፃፀም ሁኔታዎች አሉት እነሱም ተመቱዕ፤ቂራንና ኢፍራድ ናቸው።እኛ ከለንበት ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ምቹና እንዲሁም በበርካታ ዑለመዎች ዘንድ ተመራጩ «ተመቱዕ» የተባለው ነው። ስለሆነም ተመቱዕ የሚባለውን የሐጅ አደራረግ ወጥ በሆነ መልኩ እንመልከት። ተመቱዕ ማለት ምን ማለት ነው?

ተመቱዕ ማለት «ለበይክ ዑምረተን ሙተመቲዐን ቢሃ ኢለል ሐጅ» (ዑምራ አድርጌ ተፈትቼ

እስከሐጅ ድረስ ነፃ ልሆን አቤት (ለበይክ) ብያለሁ) ብሎ ለዑምራ ኢሕራም ማድረግ፤ ዑምራ አድርጎ ከዑምራ መፈታትና ከዚያም በዙልሒጃ ስምንተኛ ቀን በአዲስ መልኩ ካለንበት ሥፍራ

ሆነን ለሐጅ ኢሐራም ማድረግ ማለት ነው። ይህ ከገባን ቀጥሎ ከቤታችን ጀምረን ሐጅ እስኪ ጠናቀቅ ድረስ የለውን ሒደት አጠር ባለመልኩ አንድ ባንድ ለመመልከት እንሞክር። ሐጅ አድራጊው ከቤቱ ከመውጣቱ በፊት ገላውን ይታጠባል። የብብቱንና የብልቱን ፀጉር አድጎ ከሆነ እንዳስፈላጊነቱ ያስወግዳል። ጥፍሩንም እንዲሁ የቆርጣል። ወንድ ከሆነ ሁለት ነጭ ፎጣዎችን
ያዘጋጃል። ሴት ከሆነች ግን፤ሁሌም የምትለብሰውን መደበኛ ልብስ ነው የምትለብሰው። ባይሆን የፊት መሸፈኛ (ኒቃብ)ና ጓንት መልበስ የለባትም። ሐጅና ዑምራ ላይ ክልክል ነው። ከዚያም በመቀጠል ሐጃጁ ወደ አውሮፕላን ማረፊያ
ያመራል። አውሮፕላን ማረፊያው ውስጥ የጉዞ ፕሮሰሱን ከጨረሰ በኋላ ወደ ውስጥ ይገባል። ወደ ውስጥ እንደገባ ውዱዕ

ከሌለው ውዱዕ አድርጎ ወንዱ መደበኛ ልብሱን በፎጣዎቹ የቀይራል:: የሴቷ አለባበስ ግን አይለወጥም ወንዱ ፎጣውን ሳይሆን ገላውን ሸቶ መቀባት ይወደድለታል:: ሴቷም ቢሆን ሽታው ጎልቶ የማይወጣ ሽቶ ብትቀባ ችግር የለውም:: ከፈለጉ ቤታቸው ውስጥም አድርገው መውጣት ይችላሉ:: ከዚያም አውሮፕላን ማረፊያው ውስጥ በተዘጋጀው የሰላት መስገጃ ስፍራ ሁለት ረከዓ የኢሕራም ሰላት ወይም ሱነተል ውዱዕ ይሰግድና ዑምራን በቀልቡ ነይቶ በምላሱ «ለበይክ ዑምረተን» ይላል :: ከፈለገም ኒያውን አውሮፕላን ውስጥ ከገባም በኋላም ማድረግ ይችላል:: ከዚህ በኋላም «ለበይክ! አላሁመ! ለበየክ ላሸሪከ ለከ ለበይክ! ኢነልሐምደ ወኒእመተ ለከወልሙልክ ላሸሪከ ለከ ይላል:: ይህን ተለቢያ ጠዋፍ እስኪጀምር ድረስ በተቻለ መጠን ደጋግሞ ማለት ሱና ነው:: ወንዶች ድምፃቸውን ከፍ

አደርገው ሲሉ ሴቶች በዝቅተኛ ድምፅ ይሉታል:: ሐጅ አድራጊው መካ እንደደረሰ ጓዙን አስቀምጦ ከፈለገም ትንሽ እረፍት ወስዶ ገላውን ታጥቦ ተልቢያ እያለ ወደ ካእባ ያመራል::

ወንዱ፣ የቀኝ ትከሻውን ክፍት በማድረግ ሁለቱን የፎጣዎች ጫፍ ግራ ትከሻው ለይ ይደራርባቸዋል:: በፎጣም ይሁን በሌላ ነገር ራሱን መሸፈን ለወንድ የተከለከለ ነው::

ጠዋፍ ለማድረግ ጦሐራ መሆንና ውዱዕ ማድረግ ሸርጥ ነው:: መስጅደል ሀረም እንደ ደረሰ በቀጥታ ወደ መስጂድ በመግባት ሃጀረል አስወድ ያለበትን አቅጣጫ ፈልጎ ከቻለ ሃጀሩን መንካትና መሳም ካልቻለ ደግሞ በድንጋዩ ትክክል ሆኖ በአንድ እጁ ለሃጀሩ ሰላምታ በመስጠት፤ «ቢስሚላሂ አላሁ አክበር» በማለት ጠዋፉን ይጀምራል:: ሃጀሩል አስወድን በእጁ መንካቱና መሳሙን ወይም በሩቁ «ቢስሚላሂ አላሁ አክበር» ብሎ ሰላምታ መስጠቱን

በእያንዳንዱ ዙር ላይ ይደግመዋል:: የጠዋፍ

መነሻ ሃጀሩል አስወድ ሲሆን መድረሻው እዚያው ነው:: ከተቻለ ከሃጀሩል አስወድ በፊት ያለውን የቤቱን ጠረዝ (ሩክኑል የማኒን) በየዙሩ በእጅ መንካት ሱና ነው:: በሁለቱ ማዕዘናት መካከል «ረበና አቲና ፊዱንያ ሀሰነተን ወፊል አኺረቲ ሐሰነተን ወቂና ዐዛበ ናር» (ጌታችን ሆይ! በምድረ-ዓለም መልካም ነገር ፤በመጪውም ዓለም ደግን ነገር ስጠን) ብሎ ዱዓ ማድረግ ይወደዳል:: በእንዲህ አይነት መልኩ ሰባት ዙር ይዞራል:: ለወንዶች ብቻ የመጀመሪያውን ሶስት ዙር ክፍተት ካገኙ ዱብ ዱብ ማለት ተወዳጅ ነው::ከዚያም ወንዱ የገለጠውን ትከሻውን ሸፍኖ፤ ሴቷም ባለችበት ሁኔታ ላይ ሆና ከተቻለ ከመቃሙ ኢብራሂም ኋላ ካልተቻለ በየትኛውም ስፍራ ላይ ሁለት ረከአ ሶላት ይሰግዳሉ:: በመጀመሪያው ረከዓ ላይ ከፋቲሃ በኋላ «ቁል ያአዩሀል ካፊሩን» እና

በሁለተኛው ረከዓ ደግሞ «ቁልሁወላሁ አሀድ»ን ይቀራል

::ከዚያ ሀጃጁ ዘምዘም በደንብ ጠጥቶ ወደ ሰፋና መርዋ ያመራል:: ከዚያ ሰፋ ኮረብታ ላይ ይወጣና

ካዕባን ማየት የሚችልበት ቦታ ላይ ቆሞ ካዕባን ይቅጣጫል:: ከዚያ «አላሁ አክበር፤ አላሁ አክበር፤

አላሁ አክበር! ላኢላሀኢለላህ ወሕደሁ ለሸሪከለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምድ ወሁወ ዓለኩሊሽይኢን

ቀዲር ላኢላሀኢለላሁ ዋሕደሁ አንጀዘ ወዕደሁ ወነሰረ ዐብደሁ ወሀዘመል አህዘበ ወህደሁ» ይልና የፈለገውን ዱአ የደርጋል::

ይህንን ዚክር ሦስቴ ይደጋግመዋል::

በየመሀሉ የፈለገውን ዱዓ ያደርጋል።
ከዚያ ከሰፋ ኮረብታ ረጋ ብሎ በመውረድ ወደ መርዋ ያመራል። አረንጋዴ መብራት የበራበት ቦታ ሲደርስ ሌላኛው አረንጓዴ መብራት አጠገብ እስኪደርስ ድረስ ክፍተት ካገኘ በደንብ ይሮጣል። ይህ ሩጫ ሴቶችን አይመለከትም ከዚያ ዝግ ብሎ ወደ መርዋ ኮረብታ ይወጣል መርዋ ላይ ከወጣ በኋላ ካዕባን ተቅጣጭቶ ሶፋ ላይ ያደረገውን ዚክር ያደርጋል። በየመሃሉም የፈለገውን ዱዓ ያደርጋል።

ከዚያ ዝግ ብሎ ወደ ሶፋ ያመራል አረንጓዴው መብራት አጠገብ ሲደርስ ልክ እንደመጀመሪያው ይሮጣል።
ሌላኛው አረንጓዴ መብራት አጠገብ ሲደርስ ዝግ ብሎ ሰፋ ላይ ይወጣና፤መጀመሪያ እንዳደረገው ያደርጋል። በዚህ አይነት ሰባት ዙር ይሞላል። ከሰፋ ወደ መርዋ ያደረገው ጉዞ አንድ ሲባል ከመርዋ ወደ ሰፋ

የተመለሰው ሁለት ተብሎ ይቆጠራል:: ዙሩ ሰፋ ላይ ተጀምሮ መርዋ ላይ ይጠናቀቃል:: ከዚያ ወንዱ ፀጉሩን ሙሉ በሙሉ ይላጫል፤ ወይም ያሳጥራል::

ሴቷ ደግሞ ከሹሩባዋ ጉንጉን ከአንዱ ጫፍ ላይ የጣቷን ጫፍ ያህል ትቆርጣለች፤ ወይም ከአጠቃላይ ፀጉራ የአንድ ጣት ጫፍን ያህል ትቆርጣለች:: ሐጃጁ በዚህ ተግባሩ ከዑምራ ስራው ይፈታል:: ክልክል ሆነውበት የነበሩ ነገሮች ሁሉ ይፈቀዱለታል:: ነፃ ነው:: ለምሳሌ የተሰፋ ልብሶችን መልበስ ፡ ኮፍያ ጥምጣም ማድረግ፤ ከባለቤቱ (ቷ) ጋር የግብረስጋ ግንኙነት መፈፀም፤ ጥፍር መቁረጥ ፤ኒቃብ ጓንት (ለሴቶች) ... ወዘተ.

ከዚያ የዙልሂጃ ስምንተኛ ቀን ላይ፤ እንደገና ለሐጅ ዝግጅት ያደርጋል:: ልክ አገር ቤት እያለ እንደተዘጋጀው አይነት ዝግጅት ማለት ነው:: ለምሳሌ:- ገላውን መታጠብ፤ ጥፍሩን መቁረጥ፤ ሽቶ መቀባት፤ሶላት መስገድ፤

ወዘተ። ከዚህ ቀጥሎ ወንዱ ልብሶቹን አውልቆ ፎጣውን ለብሶ፤ሴቷ የወትሮ አለባበሷን ለብሳ (ኒቃብና ጓንት ሲቀር)
ካሉበት ማረፊያ ላይ ሆነው ለሐጅ«አላሁመ ለብበይክሐጀን» በማለት ኢሕራም ያደርጋሉ። ከዚያም ወደ ሚና ያመራሉ። ሚና ላይ ዙሕርን ፤ ዐስርን ፤ መግሪብን፤ ዒሻንና ሱብሂን በወቅታቸው ይሰግዳሉ። ባይሆን ዙሕርን ፤ ዐስርንና ዒሻን ሁለት ሁለት ረከዓ ብቻ ነው የሚሰግዱት። በዘጠነኛው ቀን (የዓረፋ እለት) ጠዋት ፀሐይ ከወጣች በኋላ ወደ ዐረፋ ምድር ይጓዛሉ። ዓረፋ ክልል ከገቡ በኋላ ዓረፋ ላይ በዙሁር ወቅት ዙሁርንና ዐስርን ሁለት ሁለት ረከአ አድርገው ይሰግዳሉ። ከዚያ ወደ ቂብላ አቅጣጫ ዙረው ሁለት እጃቸውን አንስተው ፤በየግላቸው የፈለጉትን ዱዓ በፈለጉት ቋን ቋ ያደርጋሉ። በየመሃሉ ከፈለጉ ተልቢያ፤ ተክቢራና ሌሎችንም ዚክሮች ያደርጋሉ። ቁርአንም

ወዳእ) አድርገን የመውጣት ግዴታ እንዳለብን ልንዘነጋ አይገባም:: የጠዋፍ አደራረጉ ከ10ኛው እለት ጠዋፍ ጋር ተመሳሳይ ነው:: ጠዋፉን የምናደርገው መደበኛ ልብሳችንን ለብሰን ነው:: ባይሆን ሰፋና መርዋ ላይ ሠዕይ ማድረግ የለብንም:: እንግዲህ የሐጃችን ሥራ እዚህ ላይ ይፈፀማል::

በመጨረሻም አላህ(ሱ.ወ) ሐጃችንን የተባረከ ሥራችንን የተመሰገነ ያድርግልን የአላህ ሰላምና ውዳሴ በነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በሰሀባዎቻቸውና እንዲሁም የሳቸውን ፈለግ በተከተለ ላይ ሁሉ ይሁን አሚን !!

ተፈፀመ

ሸዋል 1432

መስከረም 2004

አ.አበባ ኢትዮጵያ

ቀን ላይ ነው። ባይሆን ጠዋፉንና ሰዕዩን ከ10ኛ ው ቀን በኋላም ማድረግ ይቻላል።

በ11ኛው ቀን ዙሁርን ከሰገድን በኋላ ሃያ አንድ (21) ጠጠር በመያዝ ወደ ጀመራት እንሄዳለን። ሶስቱም የጠጠር መወርወሪያ ሥፍራዎች ላይ ከትንሹ ጀምረን እስከ ትልቁ ድረስ በቅደም ተከተል ሰባት ሰባት ጠጠሮችን ከተክቢራ ጋር እንወረውራለን። አንደኛውንና ሁለተኛውን ጉድጓድ ከወረወርን በኋላ ወደኋላ ፈንጠር ብለን ወደ ቂብላ ዞረን ዱዓ ማድረግ የተወደደ ነው።

በ12 ኛውም ቀን እንደዚሁ እናደርጋለን። ምናልባት የሚያስቸኩል ጉዳይ ከገጠመን ጓዛችንን ጠቅልለን ፀሀይ ከመግባቷ በፊት ከሚና መውጣት እንችላለን። ካልቸኮልን ግን ሚና አድረን 13ኛውን ቀን ከዙሁር በኋላ ጉድጓዶቹ ላይ ወርውረን በቀጥታ የሚናን ምድር ለቀን እንወጣለን። ከዚህ በኋላ ወደ ሃገራችን መመለስ ከፈለግን ወይም ወደ መዲና የምንሄድ ከሆነ የመሰናባቻ ጠዋፍ (ጠዋፈል

ዘንድ በመምጣት ሰባት ጠጠር በተናጠል ከእያንዳንዱ ጠጠር ጋር «አላሁ አክበር» እያሉ ይወረውራሉ፡፡ ጠጠር መወርወር ከመጀመሩ በፊት ተልቢያው ያበቃል፡፡ ከዚያ እርድ ካለባቸው ያርዳሉ (ያሳርዳሉ)፡፡ ቀጥለው፤ ወንዶች ፀጉራቸውን ይላጯሉ ወይም ያሳጥራሉ፡፡

ሴቶችም ውምራ ላይ እንዳሳጠሩት ያሳጥራሉ፡፡ ከዚያ የግበረ ስጋ ግንኙነት ሲቀር ክልክል ሆነውባቸው የነበሩ ነገሮች ሁሉ ይፈቀዱላቸዋል፡፡ ከዚያም ወደ መካ በመሄድ እንደመጀመሪያው ዓይነት ጠዋፍ ያደርጋሉ፡፡ ይህ ጠዋፍ ከመጀመሪያው ጠዋፍ የሚለየው ትከሻ መግለጥና ዱብ ዱብ ማለት የሌለው በመሆኑ ብቻ ነው፡፡ ከጠዋፍ ቀጥሎ መቃሙ ኢብራሂም ኋላ ሁለት ረከአ ይሰግዳሉ፡፡ በመቀጠልም ዘምዘምን በደንብ ጠጥተን ሰፋና መርዋ ላይ ሰዕይ አድርገን ለአዳር ወደ ሚና እንመለሳለን፡፡ ይህ ሁሉ የሚከናወነው በ10ኛው

መቅራት ይችላሉ።በአጠቃላይ እለቱን በኢባዳ አድምቀው ያሳልፉታል።
ከዙሁር በኋላ እስኪነጋ ድረስ ባለው ወቅት ዓረፋ ላይ ያልተገኘ ሰው ሐጁ ተቀባይነት የለውም።
ምሽት ፀሀይ እንደገባች በዝግታ ተልቢያ እያሉ ወደ ሙዝደሊፋ ያመራሉ። ሙዝደሊፋ እንደደረሱ መግሪብና ዒሻን በአንድነት አድርገው ይሰግዳሉ። መግሪብ ሶስት ረከዓ ሲሆን፤ዒሻ ሁለት ረከዓ ነው። በሁለቱም መሃል የሚሰገድ ሱና ሰላት የለም።
ሕፃናት፤ አዛውንት ፤ አካል ጉዳተኞችና ደካማዎች ሙዝደሊፋ ጥቂት ቆይተው፤ በሌሊት ወደ ሚና በማምራት ቀደም ብለው ጠጠር መወርወር ይችላሉ።
ችግረ የሌለባቸው ሰዎች ግን ሙዝደሊፋ አድረው ሱብሂ በመስገድ ሙዝደሊፋ ላይ ጠጠር ለቅመው ፀሀይ ለመውጣት ትንሽ ሲቀራት፤ ተልቢያና ተክቢራ እያሉ ወደ ሚና ያመራሉ። ከዚያም ጀምረተል ዓቀባ